መልእክት ስድስት

## በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዮሐ. 21፥15-17፤ ሐዋ. 20፥28፤ 1 ጴጥ. 5፥2፣ 4፤ ኤፌ. 4፥16

I. **ዛሬ በጌታ ምላሳ የእረኝነት አንገብጋቢ አስፈላጊነት አለ።**

II. **በእረኝነት መንከባከብ ማለት ለመንጋው ሁሉን-ያካተተ ለስላሳ እንክብካቤ መስጠት ነው—ዮሐ. 21፥15-17፤ ሐዋ. 20፥28፦**

ሀ. እረኝነት በጎቹ ለሚያስፈጋቸው ነገሮች ሁሉ ግድ መሰኘትን ያመለክታል።

ለ. ሁሉም በጎች በቂ አቅርቦት እና ጥሩ እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል።

III. **ክርስቶስ መልካሙ እረኛ፣ ታላቁ እረኛ፣ የእረኞች አለቃ እና የነፍሳችን እረኛ ነው—ዮሐ. 10፥9-17፤ ዕብ. 13፥20-21፤ 1 ጴጥ. 5፥4፤ 2፥25፦**

ሀ. እንደ መልካሙ እረኛ፣ ጌታ ኢየሱስ ሕይወት እንዲሆንልንና እንዲበዛልን መጣ—ዮሐ. 10፥10-11፦

1. በጎቹ ዞዌ ሕይወቱን፣ መለኮታዊ ሕይወቱን ይካፈሉ ዘንድ ለእነርሱ ቤዛነትን ለመፈጸም የነፍስ ሕይወቱን፣ የሰብዕና ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ—ቁ. 11፣ 15፣ 17።
2. የራሱን በጎች ከበረት አውጥቶ፣ እርሱን በነጻነት ወደሚበሉበት እና በእርሱ ወደሚመገቡበት፣ መሰማሪያ፣ የመመገቢያ ስፍራ ወደ ሆነው ወደ ራሱ ውስጥ ይመራቸዋል—ቁ. 9።
3. ጌታ በእረኝነቱ አይሁድ እና አሕዛብ አማኞችን አንድ መንጋ (ቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ አካል) አድርጎ ሠርቷቸዋል—ቁ. 16።

ለ. "በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን" እግዚአብሔር ከሞት አስነሣው—ዕብ. 13፥20፦

1. ዘላለማዊው ኪዳን በእረኝነት አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ማጠናቀቅ ነው።
2. ዘላለማዊው ኪዳን፣ መንጋን፣ የክርስቶስን አካል የምታመጣውንና በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን ቤተ ክርስቲያንን ለማግኘት የሆነው አዲሱ ኪዳን ኪዳን ነው።

ሐ. እንደ የእረኞች አለቃ፣ ክርስቶስ በአብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች በኩል መንጋውን በእረኝነት ይንከባከባል—1 ጴጥ. 5፥4፦

1. ያለ ሽማግሌዎች እረኝነት ቤተ ክርስቲያን ልትገነባ አትችልም።
2. የሽማግሌዎች እረኝነት የክርስቶስ በእነርሱ በኩል በእረኝነት መንከባከቡ መሆን አለበት።

መ. እንደ የነፍሳችን እረኛ፣ እስትንፋሳዊው ክርስቶስ ለውስጥ ማንነታችን ሁኔታ ግድ በመሰኘት ውስጣዊ ሁኔታችንን ይቆጣጠራል—2፥25፦

1. ለነፍሳችን ደኅንነት ግድ በመሰኘት እና የውስጥ ማንነታችንን ሁኔታ በመከታተል በእረኝነት ይንከባከበናል።
2. ነፍሳችን እጅግ ውስብስብ ስለሆነች፣ አእምሮአችንን፣ ስሜታችንን እና ፈቃዳችንን እና ችግሮቻችንን፣ የሚያስፈልጉንን ነገሮች እና ቁስሎቻችንን ለመንከባከብ፣ ነፍሳችንን በእረኝነቱ ይንከባከብ ዘንድ ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ የሆነው በመንፈሳችን ውስጥ ያለው ክርስቶስ ያስፈልገናል።

IV. **በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት ለመንከባከብ፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን፣ በእግዚአብሔር መቀናበር፣ እግዚአብሔርን መኖር፣ እግዚአብሔርን መግለጥ፣ እግዚአብሔርን መወከል እና እግዚአብሔርን ለሌሎች ማገልገል ያስፈልገናል፦**

ሀ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆናችንን እና በእግዚአብሔር መቀናበራችንን ይጠይቃል—ዮሐ. 14፥20፤ 1 ቆሮ. 6፥17፤ ኤፌ. 3፥17፤ ቆላ. 3፥10-11።

ለ. እግዚአብሔርን የሚኖሩ ብቻ በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት ሊንከባከቡ ይችላሉ—ፊልጵ. 1፥21።

ሐ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ እርሱን እንገልጠው ዘንድ ራሱን እንደ ሕይወታችን ወደ ውስጣችን መሥራት ነው—ዘፍ. 1፥26፤ ኤፌ. 1፥11፤ 3፥11፤ 2 ጢሞ. 1፥9።

መ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት እንደሚንከባከቡ ሰዎች፣ እግዚአብሔርን መወከል እና እንደ እግዚአብሔር ወኪል ማገልገል ያስፈልገናል—2 ቆሮ. 1፥3-4፣ 12፣ 15-16፤ 2፥10፤ 10፥11፤ 11፥2።

ሠ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ እግዚአብሔርን ለሌሎች ማገልገል ነው፦

1. እግዚአብሔርን ለሌሎች ማገልገል የምንችልበት መጠን፣ ሕይወት [በእኛ] ሞልቶ ይፈስ ዘንድ በእግዚአብሔር በመሰበራችን ላይ ይመረኮዛል—4፥10-12፣ 16፤ ዕብ. 4፥12።

2. አንዳችን ለሌላችን እግዚአብሔርን ማገልገል ከፈለግን፣ ወደ ማንነታችን ውስጥ የተሠራውን በሂደት ያለፈውን አምላክ በማገልገል የጸጋን፣ የእውነትን፣ የመንፈስን እና የሕይወትን ቃላት መናገር ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፥16-17፤ 4፥25፣ 29፤ ዮሐ. 6፥63።

**V. ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን መንጋ በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት እንዲንከባከቡ ሽማግሌዎችን አዘዛቸው—1 ጴጥ. 5፥2፡-**

ሀ. *በእግዚአብሔር መሠረት* ማለት እግዚአብሔርን መኖር አለብን ማለት ነው።

ለ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ስንሆን፣ እግዚአብሔርን እንሆናለን፣ ሌሎችን በእረኝነት በመንከባከባችንም ውስጥ እግዚአብሔር ነን።

ሐ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ በምርጫችን፣ በፍላጎታችን፣ በዓላማችን እና በግል ጸባያችን መሠረት ሳይሆን በእግዚእብሔር ባሕርይ፣ ፍላጎት፣ መንገድ እና ክብር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ ነው።

መ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ እግዚአብሔር በባሕርያቱ በሆነው መሠረት በእረኝነት መንከባከብ ነው።

ሠ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት ለመንከባከብ፣ በሕይወት፣ በባሕርይ፣ በመግለጥ እና በአገልግሎት እግዚአብሔርን መሆን ያስፈልገናል፡-

1. የመለኮታዊው ሕይወት ጥቅል ድምር፣ ብሎም መለኮታዊውን ሕይወት ራሱን እንሆን ዘንድ ሦስታንዱን አምላክ እንደ ምንጭ፣ እንደ ፍልቅ እና እንደ ወንዝ በመደሰት በመለኮታዊው ሕይወት ፈጽመን መሞላት ያስፈልገናል—ዮሐ. 4፥14፤ ቆላ. 3፥4።
2. በፍቅር፣ በብርሃን፣ በጽድቅ እና በቅድስና ባሕርያቱ እግዚአብሔርን መሆን ያስፈልገናል።
3. በእረኝነታችን እኔነትን ከግል ጸባዩ እና ከልዩ ባሕርያቱ ጋር ሳይሆን እግዚአብሔርን እንድንገልጥ የክርስቶስ ርቢ፣ የእግዚአብሔር መገለጥ መሆን ያስፈልገናል።
4. እግዚአብሔር በሆነው ነገር መሠረትና በኢኮኖሚው ባለው ግቡ መሠረት ለመንጋው በሚሰጠው የእረኝነት አገልግሎቱ እግዚአብሔርን ልንሆን ያስፈልገናል።

**VI. የክርስቶስን አካል የሚገነባው እረኝነት የእርስ በርስ እረኝነት ነው—1 ቆሮ. 12፥23-26፡-**

ሀ. ሁላችንም ሌሎችን በእረኝነት ለመንከባከብ በክርስቶስ ሕይወታዊ እረኝነት ሥር መሆን እና ከእርሱ ጋር አንድ መሆን ያስፈልገናል—ዮሐ. 21፥15-17።

ለ. የሕይወት እድገት ደረጃቸው ምንም ቢሆን አማኞች ሁሉ እረኝነት ያስፈልጋቸዋል።

ሐ. ሁላችንም እንከኖች እና እጥረቶች አሉን፣ ሌሎች በእረኝነት እንዲንከባከቡንም ያስፈልገናል።

መ. እርስ በርስ የእረኝነት እንክብካቤ የምንሰጥ እና የእረኝነት እንክብካቤን የምንቀበል በጎችም እረኞችም ነን።

ሠ. በዚህ የእርስ በእርስ እረኝነት በኩል፣ አካሉ ራሱን በፍቅር ያንጻል—ኤፌ. 4፥16።

*© 2026 Living Stream Ministry*